# ሰዎቹን ምን ነካቸው?

ሳዶር ( ከድሬዳዋ)

ይህን ትዝብት አዘል ፅሁፍ ለማፍ ያነሳሱኝ ነገሮች ህዳር 22/2002 በማኅናዘሪያ ጋዜጣ ላይ የተስተናገዱት የመድረክ አመራር አባል አቶ ገብሩ አሥራት ጋር የተደረገው ቃለ ማጠይቅና ዶክተር ሃይሉ አርአያ የብሔር ብሔረሰቦችን ቀን አስሜልከተው ለአዲስ አድማስ ጋዜጣ የሰጡት አስተያየት ነው፡፡

አቶ ገብሩ አሥራት ከማኅናዘሪያ ጋዜጣ ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ በርካታ ነገሮችን የዳሰሱ ቢሆንም የኔን ትኩረት የሳበው ግን የመድረክ አባል ፓርቲዎች በመድረክ ማኒፌስቶ ላይ ያላቸውን አቋም አስሜልከተው የተናገሩት ነገር ነው፡፡ የመድረክ አባል ድርጅቶች በበርካታ ጉዳዮች ላይ ማስማማታቸውን ይገልፁና "ከሁለት አንቀፆች በስተቀር በሁሉም ላይ ተስማምተናል" ይላሉ፡፡

አቶ ገብሩ "ሁለት አንቀፆች ብቻ" በማለት እንደ ዋዛ ለማለፍ የሞከሩት የብሔር ብሔረሰቦች ጉዳይና የሜሬት ጥያቄን ነው፡፡ ሰወየወን ምን ነካቸው? ለመሆኑ በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ቁልፍ ጥያቄዎች በሆኑት የብሔር ጥያቄና የሜሬት ጉዳይ ላይ አንድ አቋም ማያዝ ያልቻለ ስብስብ እንዴት በሌሎች ጉዳይ ላይ አንድ ሆኖ ጠንካራ ተፎካካሪ መሆንና የህዝብን ድጋፍ ማግኘት ይቻለዋል ?

ከ80 በላይ ብሔር ብሔረሰቦች በሚኖሩባት ሃገራችን የብሔር ጥያቄ አንገብጋብና አነጋጋሪ ሆኖ የኖረና ያለ ጉዳይ ነው፡፡ በሀገራችን ምንም እንኳን በርካታ የፖለቲካ ፓርቲዎች ቢኖሩም ለብሔር ጥያቄ ቦታ የሚሰጡት ግን ጥቂቶች ናቸው፡፡ በተለይም ቅንጅት፣ አንድነት፣ መድረክ ወዘተ… በሚሉ ስሞች በየጊዜው የሚደራጁ ቡድኖች፣ ፓርቲዎችና ስብስቦች ለብሔር ጥያቄ የሚሰጡት ቦታ አነስተኛ ከመሆኑም በላይ በታታኝ ወይም ጊዜ ጠብቆ እንደሚፈነዳ ፈንጂ ሲማስሉት አሊያም አከሳሪ የፖለቲካ አጀንዳ አድርገው ሲቆጥሩት ይታያሉ፡፡

በተለይም በምርጫ 97 የተፈጠረወና የፓርቲዎች ስብስብ የነበረው የቀድሞው ቅንጅት በብሔር ጥያቄ ላይ ግልፅ አቋም ካለማያዙም በላይ በተለያዩ መድረኮች ብሔርን መሠረት ያደረጉና ግልፅ የሆኑ በተወሰኑ ብሔሮች ላይ ያነጣጠሩ የጥላቻ ቅስቀሳዎችን ያደርግ እንደነበረ የቅርብ ጊዜ ትወስታችን ነው፡፡ ይህም በቀላሉ የማይገመት ተቃወሞን በህብረተሰቡ ላይ በመፍጠሩ ፓርቲወን ለሽንፈት ከመዳረጉም በላይ ለቅንጅቱ ማብታተን ከፍተኛ አስተዋፅኦ ነበረው የሚሉ በርካቶች ናቸው፡፡ እኔም በኢትዮጵያ የብሔር ጉዳይን ከሌሎች መሠረታዊ ጥያቄዎች ነጥሎ ማየት አያዋጣም የሚል እምነት አለኝ፡፡

ዛሬ ከአምስት ዓመታት በኋላም የመድረክ አቋሞችን ለተመለከተ አንዳንዶቹ ተቃዋሚዎች ዛሬም ከስህተታቸው እንዳልተማሩ ዛሬም እንደትናንቱ ጉዳዩን ብዙም አንገብጋቢ አጀንዳ እንዳልሆነ አለባብሰው በማለፍ ላይ መሆናቸውን ነው ከአቶ ገብሩ ንግግር የምንረዳው፡፡ ስምንት የፖለቲካ ፓርቲዎችን ያቀፈውና ራሱን "መድረክ" ብሎ የሰየመው ስብስብ በኢትዮጵያ ተንሠራፍተው ያሉትን ፈርጀ ብዙ ችግሮች ለማስወገድና በተቃዋሚ ፖለቲካ ድርጅቶች ዙሪያ ያለውን ተባብሮ ያለማስራት ድክመትን ለመቅረፍ መቋቋሙን ቢገልፅም የብሔር ጥያቄን ግን አለባብሶ ያለፈበት ሁኔታ ነው ያለው፡፡

"መድረክ" ምንም እንኳን በውስጡ በብሔር የተደራጁ ፓርቲዎች ማቀፉን ቢገልፅም ፓርቲዎቹ በብሔር ጉዳይ ላይ ግን አንድ አቋም ሳይዙ ነው ዛሬ ላይ የደረሱት፡፡ የቀድሞውን "ቅንጅት"ን የፈጠሩት ፓርቲዎችና አንድ ሳይሆኑ አንድ የሆኑ እየመሰላቸው አንዳች ነገር አጣበቋቸው ወደ ምርጫ ቢገቡም ብዙም ሳይቆዩ ነበር ብትንትናቸው የወጣው፡፡ የዛሬው የፖለቲካ ስብስብ "መድረክ" ቁልፍ በሆኑ መሠረታዊ ጥያቄዎች ላይ መስማማት ባልቻሉ ፓርቲዎች የተመሰረተ በመሆኑ ከቅንጅት ዕጣ እንዴት እንደሚያመልጥ አይገባኝም፡፡

በመድረክ ውስጥ የተደራጁት ተቃዋሚ ፓርቲዎች እንደ ቀድሞው ቅንጅት ሁሉ ዓላማቸው አድርገው የተነሱት ኢህአዴግን ማሸነፍና ስልጣን መያዝ እንጂ ሊያስተሳስራቸው የሚችል የወል አጀንዳ ይዘዋል ለማለት አይቻልም ፡፡የመድረክ አመራሮች ቀደም ሲል የተለያዩ ርዕዮተ ዓለም አራማጆች የነበሩ መሆናቸው፣ እንደ አንድነት ፓርቲ ያሉት ደግሞ በውስጥ ችግር እየታመሱ ያሉና የውስጥ ችግራቸውን ለመፍታት ሳይችሉ ቀርተው ለክፍፍል፣ ለፀብና አምባጓሮ በተዳረጉበት ወቅት ሰዎቹ ምን ያህል ርቀት አብረው ሊጓዋዙ ይችላሉ የሚል ጥያቄን እየፈጠረ ነው፡፡

ይሁንና የመድረክ አመራር የሆኑት አቶ ገብሩ አሥራት ብዙ ብዙ እያሉን ነው፡፡ አቶ ገብሩ አስራት በዚሁ ቃለ ምልልሳቸው ላይ የተሰበሰብነው ኢህአዴግን ለማሸነፍ ሳይሆን ብዙ የሚያሰባስቡን የጋራ አጀንዳዎች በመኖራቸው ነው ይሉናል፡፡ እዚህ ላይ አቶ ገብሩን አንድ ጥያቄ ልጠይቃቸው እወዳለሁ በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ትናንትም ሆነ ዛሬ ቁልፍ በሆነው የብሔር ጥያቄ ላይ አንድ ካልሆናችሁ፣ የአርሶ አደሩ የመኖር ዋስትናው በሆነው በመሬት ጉዳይ ላይ አንድ አቋም መያዝ ካልቻላችሁ በምን ጉዳይ ላይ ነው አንድ መሆን የቻላችሁት? በአሰብ ጉዳይ ላይ ነው? "በየትኛውም መንገድ ቢሆን የባህር በር እናስገኝልሃለን" የሚለው ተሰፋችሁ ከሆነ በእጃችሁ የሌለና ኢትዮጵያን ዳግም ወደ ጦርነት የሚከት አጀንዳ በመሆኑ ብዙም የሚያዋጣ አይመስለኝም፡፡ በጣም የተረጋጉና አስተዋይ መሆናቸው የሚነገርላቸው ዶክተር ሃይሉ አርአያም ሰሞኑን ለአንድ ጋዜጣ የሰጡት አስተያየት አስገርሞኛል፡፡

እኚህ ሰው የብሔር በሔረሰቦች ቀንን አስሜልከተው ሲናገሩ" የብሔር ብሔረሰቦች በዓልን ማክበር የጀመሪው ደርግ ነው" ማለታቸውን አንብቤያለሁ የአፍ ወለምታ፡፡ እኚህ ሰው ምን ነካቸው? እኔ መቼም እንደ እሳቸው ዕድሜ ጠገብ ባልሆንም የደርግን ስርዓት ደርሼበታለሁና ይህ አባባላቸው አልተዋጠልኝም፡፡ ምክንያቱም ደርግ የብሔር ብሔረሰቦችን በዓል ሲያከብር ተሰምቶም ታይቶም አይታወቅምና፡፡ ምናልባት ደርግ በየአመቱ ያከብረው ከነበረው የአብዮት በዓል ጋር ተጋጭቶባቸው ይሆን? እንደኔ እንደእኔ ደርግ በዓሉን መቼ እና የት እንዳከበረ አብረው ቢነግሩን ደስ ባለኝ ነበር "የበሬውን ምሥጋና ወሰደው ፈረሱ" እንደሚባለው ሆነና በህዝቦች ማስዋእትነት የተገኘውን የእኩልነት መብትና ሆነ ይህን መብት ያረጋገጠውን ህገ መንግስት ለማዘከር የተዘጋጀን በዓል ለደርግ ማስጠቱ ምን ለማግኘት እንደሆነ አልገባኝም፡፡

ዶክተር ሃይሉ ለመሆኑ በእናንተ ዘመን ልጆች በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ይማሩ ነበር? ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች በልጆቻቸው ይተዳደሩ ነበር? ዜጎች በየትኛውም የአስተዳደር እርከን ከአማርኛ ቋንቋ ወጪ የሚጠቀሙበት ጊዜና አጋጣሚ ነበር? ብሔር ብሔረሰቦች በባህላቸው፣ በቋንቋቸው፣ ብሎም በማንነታቸው የሚኮሩበት ዘመን ነበር? እኚህ ሰው ትንሽ ቆየት ብለው የብሔር ብሔረሰቦች እኩልነትና ነፃነት ማክበር የጀመሪው በደርግ ጊዜ ነው ሳይሉን አይቀርም፡፡ ይህ አባባላቸው አዲሱ የዴሞክራሲያዊ ስርአት ለብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች መብትና እኩልነት ማክበር ላበረከተው አስተዋፅኦ ማግኘት የሚገባውን እውቅና ላለማስጠት ወይስ ባልሰሩት ስራ ለመወደስ ሜፈለግ? በምኒልክ ጊዜ የደነቆረ "ምኒልክ ይሙት" እያለ ሲምል ይኖራል እንደሚባለው ሁሉ ከደርግ ጋር የቆረቡ እስኪያስማስልባቸው ድረስ ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ ደርግን ለማወደስ ሲሉ ያልነበረ ነገር ማናገር "ነገ አገር እንመራለን" ከሚሉ ሰዎች የሚጠበቅ ነገር አይደለም፡፡